## በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

# የቅርስ ጥበቃ፣ ጥገናና እንክብካቤ

## መመሪያ ቁጥር 483/2013

መስከረም 2010 ዓ.ም.

# የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

# የቅርስ ጥበቃ፣ ጥገናና እንክብካቤ

# መመሪያ ቁጥር 483/2013

የሀገራችንን የታሪክና የባህል ቅርሶችን በመንከባከብ፣ ሊደርስባቸው ከሚችሉ አደጋዎች በመጠበቅ፤ ጉዳት የደረሰባቸውን በመጠገንና በመንከባከብ ለቅርሱ ባለቤቶች፣ ለቅርሱ አካባቢ ማህበረሰብና ብሎም ለመላ ሀገሪቱ ህዝብ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታን እየሰጡ ወደ መጪው ትውልድ እንዲተላለፉ ለማስቻል፣

የታሪክና የባህል ቅርሶች በአያያዝ፣በአጠቃቀም እንዲሁም በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ መንስኤ ሊደርስባቸው የሚችለውን ጉዳት አስቀድሞ መከላከል አስፈላጊ በመሆኑ፣

በቅርሶች ላይ የሚደርሰውን ብልሽት ማቆም የማይቻል ሲሆን፣ የጉዳቱን መጠንና ፍጥነት ለመቀነስ ታሪካዊ ይዘቱ ሳይለውጥ እና የቅርስ እሴታቸው ሳይሸራረፍ በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመስርቶ እንደ ጉዳቱ መጠን እርምጃዎችን በተገቢው ጊዜና ወቅት መውሰድ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ዓለም አቀፉን የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ መርህዎችንና ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ ሁኔታ የቅርስ ጥበቃ፣ እንክብካቤና ጥገና ተግባራትን መምራት በማስፈለጉ፣

የቅርስ ጥበቃ፣እንክብካቤና ጥገና ተግባርን ብቃት ባላቸው ባለሞያዎች የቅርሶችን እሴት ዘለቄታዊነት በጠበቀ መልኩ በተመጣጠኝ ወጪና በጥራት በማከናወን የቅርሶችን ሕልውና ለማረጋገጥ፣

በተጨማሪም ከባለስልጣኑ ጋር በመተባበር የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ተግባር ለሚያከናውኑ የቅርስ ባለቤቶች፣ ክልሎች፣ በዘርፉ የተሰማሩ ማኅበራት እና በዘርፉ የተሰማሩ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና ባለሙያዎች መብትና ግዴታ በግልፅ ማስቀመጡ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በቅርስ ጥናትና ጥበቃ አዋጅ 209/1992፣ አንቀፅ 46 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የቅርስ ጥበቃ፣ ጥገናና እንክብካቤ መመሪያ ቁጥር 483/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በቅርስ ጥናትና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 209/92 አንቀፅ 3 የተሰጠው ትርጓሜ እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1) **"የቅርስ እሴት"** ማለት ቅርሱን የቅርስነት ዋጋ የሰጡት ጊዜ የማይሽራቸው ሥነ ውበታዊ፣ ታሪካዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ማኅበራዊና መንፈሳዊ እሴቶች ናቸው፡፡
2) **"የቅርስ አካላት"** ማለት ማንኛውም በቅርሱ ወይም በመካነ ቅርሱ ወይም በቅርሱ ቦታ ላይ የሚገኝ አካላዊ ቁስ ሲሆን ይህም የቅርሱ መሠረት፣ ምሰሶ፣ ማገር፣ ጣሪያ፣ ወራጅ፣ ይዞታ፣ ተያያዥነት ያላቸዉ እቃዎችና ቁሳቁሶችን ይጨምራል፡፡
3) **"የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ"** ማለት ቅርሶችን ከአደጋ በመከላከልና ሲጎዱም የቅርስነት እሴቱን በጠበቀ መልኩ በመጠገን ለማህበረዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በማዋል ለተተኪው ትውልድ እንዲተላለፉ ለማስቻል የሚከናወኑ ተግባራት ናቸዉ፡፡
4) **"የቅድመ መከላከል ሥራ"** ማለት ቅርሱ ወይም የቅርሱ ቦታ ላይ ቀጥታ ንኪኪ በሌለው መንገድ ቅርሱን ለመጠበቅ እና ከአደጋ ወይም ከጉዳት ለመከላከል የሚወሰድ ዕርምጃ ነው፡፡
5) **"የቅርስ ጥበቃ"** ማለት የቅርሶችን ነባራዊ ይዘትና እሴት ሳይለቅ በዘላቂነት ህልውናቸውን ለማስቀጠል በቅርሶች ዙሪያ የሚወሰዱ የመከላከል እርምጃዎችን መውሰድ ማለት ሲሆን፤ የከለላ፣ መጠለያ፣ የድጋፍ፣ የግንብና የመሳሰሉትን የቅድመ መከላከል ሥራዎችን ያጠቃልላል፡፡
6) **"የቅርስ እንክብካቤ"** ማለት ቅርሶች ነባር ይዘታቸው ሣይቀይሩ እንዲቆዩ ለማድረግ የሚከናወን የማይቋረጥ፣ የእለት ተዕለት እና ወቅታዊ የተግባርሥራ

ነው፡፡በቅርሱ እና በቅርሱ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚከናወኑ ዕለታዊና ወቅታዊ የእንክብካቤ፣ የጽዳትና የማስዋብ ሥራዎች በእንክብካቤ ውስጥ ይካተታሉ፡፡

7) **"የቅርስ ጥገና"** ማለት ቅርሶች በደረሰባቸው የሰው ሰራሽ ወይም ተፈጥሮአዊ ጉዳት ምክንያት በከፊል የወደመ ወይም የጠፋ አካላቸውን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ቀድሞ በተሰሩበት ጥሬ ዕቃ ወይም ቁስ እና በተሰሩበት የአሰራር ጥበብና ዘዴ ወደ ቀድሞ ይዞታቸው እንዲመለሱ ማድረግ ነው፡፡

8) **"የቅርስ መልሶ ግንባታ" ማለት** በከፊል የወደሙ ቅርሶችን አርኬዎሎጂካዊና የአርክቴክቸር መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ቀድሞ በተሰሩበት ጥሬ ዕቃ ወይም በአዲስ ጥሬ ዕቃ የሚካሄድ ቅርስን መልሶ መገንባት ተግባር ነው፡፡

9) **"የማጠናከር ስራ"** ማለት ቅርሶችን ለመጠበቅ ወይም ባሉበት ሁኔታ ለማቆየት በቅርሱ አካል ላይ ተጨማሪ አካል በመጠቀም ዘለቄታዊነቱን ለማረጋገጥ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡

10 **"የቅርስ ለአገልግሎት ማብቃት"** ማለት ቅርሱን ወይም የቅርስ ቦታው ነባሩን አገልግሎት እንዲቀጥል ወይም ለታቀደለት አዲስ ከቅርሱ ባህርይ ጋር ለሚስማማ አገልግሎት ለማመቻቸት የሚከናወን የማሻሻያ፣ የማስፋፊና የማስዋቢያ ተግባር ነው፡፡

11 **"የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት"** ማለት በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ የሙያ ዘርፍ በቂ እውቀት፣ክህሎትና ልምድ ላላቸው ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ነው፡፡

12 **"የሥራ ፈቃድ"** ማለት ለሚንቀሳቀሱና ለማይንቀሳቀሱ ቅርሶች ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገናሥራ ለማካሄድ ጥያቄ ላቀረቡ ወይም ላመለከቱ ባለሙያዎች ወይም ድርጅቶች በፅሁፍ የሚሰጥ ህጋዊ ፍቃድ ነው፡፡

13 **"ባለሙያ"** ማለት በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ የሙያ ዘርፍ እውቀት፣ ክህሎትና ልምድ ያለው እና በባለሥልጣኑ የተመዘገበና የብቃት ማረጋገጪያ የተሰጠው ሰው ነው፡፡

14 **"አማካሪ"** ማለት የቅርስ ጥበቃ፣ እንክብካቤና ጥገና የብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ባለው ወይም ባላቸው ግለሰቦች የሚቋቋም እና ህጋዊ የአማካሪነት ፍቃድ በማግኘት ለቅርስ ጥበቃ፣ እንክብካቤና ጥገና ፕሮጀክት ጥናት በማዘጋጀት፣ በጥገና ወቅት ስለቅርሱ ጥገና ሥራ ክትትል፣ ቁጥጥርና የምክር አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ነው፡፡

15 "**መካነ ቅርስ**" ማለት በብሄራዊ ወይም በክልል ደረጃ የተመዘገቡ ቅርሶች የሚገኙበት ሥፍራ ወይም ማንኛውም ቅርስ ወይም የቅርስ ክምችን የያዘ ቦታ ወይም መሬት ወይም መልክዓ ምድር ማለት ነው፡፡

16 "**የቅርስ ባለቤት**""ማለት በይዞታቸው ሥር የሚገኙ ቅርሶችን የሚያስተዳድር ተፈጥሮአዊ ወይም ህጋዊ ሰዉ ነዉ፡፡

17 "**ሥራ ተቋራጭ**" ማለት ከባለሥልጣኑ የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ባለው ወይም ባላቸው ባለሞያዎች ወይም የብቃት ማረጋገጫ ያላችውን ባለሞያዎች ቀጥረው የሚያሰሩ በህጋዊነት የተቋቋሙና የቅርስ ጥበቃ፣ እንክብካቤና ጥገና ለማከናወን ከባለሥልጣኑ ወይም ከቢሮዎች የሥራ ፍቃድ ያገኙ አካላት ናቸው፡፡

18 "**ቢሮው**" ማለት በዘጠኙ ክልሎችና በሁለቱ የከተማ አስተዳድሮች የሚገኙ የባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ናቸዉ፡፡

19 "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

20 ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. ዓላማ

የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ተግባር ተገቢዉን መርህ፣ የአሰራር ሥልት፣ ቅንጅታዊ አሰራርንና ሳይንሳዊ ደረጃውን በጠበቀ መንገድ እንዲከናወን በማድረግ ቅርሶቹን ወደመጪው ትውልድ እንዲተላለፉ ማስቻል ነው፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሀገሪቱ ዉስጥ በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ዘርፍ በተሰማሩ ባለሙያዎችና ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 5. የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ መርህዎች

የሚከተሉት የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ጥገና መሰረታዊ መርሆች ናቸው፡፡

1. ቅርሶች ለአደጋ እንዳይጋለጡና ለጉዳት እንዳይዳረጉ በማድረግ የቅርሶቹን እሴት መጠበቅ
2. የቅርስ ጥበቃ እንክብካቤና ጥገና ተግባር የቅርሱን አካላት፣ የቅርሱን ቦታ፣ የቅርሱን አካባቢ፣ የሚሰጠውን አገልግሎት እና ታሪካዊነቱን በመጠበቅ ማከናወን፤

3. የቅርሱን ነባራዊ ሁኔታ በማጥናት ለመጠበቅ ተገቢነት ያለውን እውቀትና ክህሎት አጣምሮ መጠቀም፤

4. የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ጥገና ተግባር ሁሉንም የቅርሱን ባህላዊና ተፈጥሯዊ እሴቶች በመገንዘብ ማከናወን፤

## ክፍል ሁለት
## ስለቅርስ ጥበቃ እንክብካቤና ጥገና

5. የባለስልጣኑና የቢሮዎች ተግባርና ኃላፊነት

1) ባለሥልጣኑና የቢሮው የሚከተሉት የጋራ ተግባርና ኃላፊነት አለባቸው፤

   ሀ. ማህበረሰቡና የቅርስ ባለቤቶች ቅርሶችን ለመጠበቅ የሚያካሂዱትን ጥረት በመደገፍ የሙያና የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፤

   ለ. ቅርሶችን ለመጠገንና ለመንከባከብ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች እንደቅርሶቹ ደረጃ የስራ ፍቃድ መስጠት፣

   ሐ. የቅርሶች ጥበቃና እንክብካቤ ፍቃድ በተሰጣቸው ተቋራጮች ሲካሄድ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤

   መ. ለቅርሶች ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ተግባር የሙያ፣ የገንዘብና የቁሳቁስ እገዛ ከተለያዩ አካላት የሚገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

   ሠ. የቅርሱን ይዞታና ድንበር በህግ የማያስከበር እንዲሁም የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን ለሚመለከታቸዉ አካላት መስጠት፤

   ረ. ሀገር በቀል የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ዕውቀቶችና ክህሎቶች በሉላዊነት፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎች ምክንያት እንዳይበረዙና እንዳይጠፉ መከላከልና መጠበቅ፤

   ሰ. ቅርሶችን በዘላቂነት ለመጠበቅ ያለውን ጥቅም ግምት ውስጥ በማስገባት በሦስተኛ ወገን ቅርስን ጠግኖ ለአገልግሎት የማብቃት ጥያቄዎች ፈቃድ መስጠት፤

2) ባለስልጣኑ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣

   ሀ. የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

   ለ. በብሄራዊነት ለተመደቡት ቅርሶች ጉዳት እንዳይደርስባቸው ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ተግባር ያከናውናል፤

ሐ. በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ተግባር የሚሰማሩ የሞያ ማህበራት እንዲደራጁ ያደርጋ፤

3) ቢሮዎች የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሯቸዋል፣

ሀ. በክልል ደረጃ ለተመደቡት ቅርሶች ጉዳት እንዳይደርስባቸው ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ተግባር ያከናውናል፤

ለ. የዘርፉ ሀገር በቀል ዕውቀቶችና ክህሎቶች እንዳይጠፉ የጥበቃ ተግባራትን ያከናውናሉ፤

ሐ. የሀገር በቀል ዕውቀትና ክህሎት ያላቸው ሙያተኞች ተደራጅተው በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ተግባራት እንዲሰማሩ ድጋፍ ያደርጋል፣

## 6. <u>ስለቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ሙያ ብቃት ማረጋገጫ</u>

1. ማንኛውም ሰው የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ተግባር ማከናወን የሚችለው በባለሥልጣኑ ተመዝግቦ በዘርፉ የሚሰጠውን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡
2. ባለሥልጣኑ በዘርፉ ለመሰማራት የሚቀርበውን የብቃት ማረጋገጫ ማመልከቻ መርምሮ ለዚሁ ተግባር ባዘጋጀው መመሪያ መሰረት ህጋዊ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በአይነትና በደረጃ ለይቶ ይሰጣል፡፡

## 7. <u>የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ሥራ ፍቃድ</u>

1) ማንኛውም ቅርስን በባለቤትነት ወይም በባለይዞታነት የያዘ ሰው ቅርሱን የመጠበቅና የመጠገን ተግባርን ለማከናወን በቅድሚያ እንደ ቅርሱ ደረጃ የቅርስ ጥበቃና አንክብካቤ-ጥገና ሥራ ፍቃድ ከሚመለከተዉ አካል ማገኘት አለበት፡፡
2) ባለሥልጣኑ የዓለም አቀፍና በብሄራዊ ደረጃ ለተመደቡት የማይንቀሳቀሱና የሚንቀሳቀሱ ቅርሶች የጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ተግባራት የሥራ ፍቃድ ይሰጣል፣
3) ቢሮዎች በክልል ቅርስነት ለተመደቡ የማይንቀሳቀሱና የሚንቀሳቀሱ ቅርሶች የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ተግባራት የሥራ ፍቃድ ይሰጣሉ፤

4) በሦስተኛ ወገን ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ወይም ጥገና ጥያቄ እንደቅርሱ የአስተዳደር ደረጃ በሚመለከተው አከላል ተገምግሞ ፍቃድ ይሰጠዋል፡፡

## 8. ስለሥራ ፍቃድ ጥያቄ አቀራረብ

1) የቅርስ ጥበቃና እንክብባቤ-ጥገና ሥራ ፍቃድ ጥያቄ በቅርስ ባለቤቶች፣ ባለይዞታዎች ወይም ሌሎች በሚመለከታቸው ሦስተኛ ወገኖች ሊቀርብ ይችላል፣
2) በባለሥልጣኑ ወይም በቢሮው በጀትና ባለሙያ እንዲከናወን የሚቀርብ ጥያቄ ለዚሁ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ቅርሱ መመዝገቡን፣ የቅርሱን ነባራዊ ሁኔታንና በአደጋ ላይ በመሆኑ አስቸኳይ ጥገና እንደሚያስፈልግ የሚገልጹ ሰነዶችን ማያያዝ ይኖርበታል፡፡
3) በራሱ በጀት የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ሥራ ለማከናወን ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት፡-

   ሀ. የቅርሱን ዓይነት፣ የጉዳቱንና መጠን፣

   ለ. ስለታቀደው የጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ሥልትና የሥራ ዝርዝር

   ሐ. በጥገናው የሚሳተፉ አካላትን የብቃት ማረጋገጫና የስራ ልምድ ማስረጃዎ በመያያዝ በዝክረ ተግባር ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

4. የሚመለከተው አካል ሥራ ፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻ በቀረበለት በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## 9. በባለሥልጣኑ ስለሚደረግ የጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ሥራ

1) ባለሥልጣኑ ከባለሞያዎቹ በዘርፉ ከተሰመሩ አማካሪዎች እና ተቋራጮች፤ ከዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በብሔራዊ ቅርስነት ለተመደቡ ቅርሶች የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ጥገና ተግባሩን ያከናውናል፡፡
2) የቅርስ ባለቤቶች ወይም ባለይዞታቸው በአቅም ማጣት ምክንያት ቅርሶቹን መጠበቅ ወይም መጠገን ካልቻሉ፡ ባለሥልጣኑ ለዚሁ ተግባር የሚያስፈልገውን የሙያና የፋይናንስ ፍላጎት ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል በመሸፍን ለቅርሶቹ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ተግባር ያከናውናል፡፡
3) ባለሥልጣኑ የቅርስ ጥበቃ፣ እንክባካቤና ጥገና ሥራዎች ሲያከናውን የቅርሱን ነባራዊ ሁኔታና የጉዳት መጠን ለመለየት፣ ለመመዝገብና

ለመሰነድ በሚያካሂቸው ተግባራት የሚመለከታቸው የባህልና ቱሪዝም ተቋማት ተገቢውን መረጃ መስጣት ይኖርባቸዋል፡፡

4) ለዘርፉ የሚያስፈልገዉ ወጪ በሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ሊሸፈን ይችላል፡፡

## 10. የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ የአሠራር ሥልቶች

ማንኛውም ቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ሥራ የሚያከናውን ሰው የሚከተሉትን ሥልቶች ሊከተል ይገባል፡-

1) ተገቢውን የቅድመ መካለከል ተግባራት በመከናወን ቅርሱ ከተፈጥሮአዊና ሰው ሰረሽ አደጋዎች መጠበቅን ያካትታል፤
2) የቅርስ ጥበቃና ጥገና ሥራ በየዕለቱና ወቅቱን ጠብቆ የሚከናወን ሲሆን የቅርሱን አገልግሎት፡ እሴትና ይዘት ባለበት የሚያስቀጥል መሆን ይኖርበታል፡፡
3) የቅርስ ጥገና ጥናትን መሰረት በማድረግ የቅርሱ አካል ሲበለሽ፡ ሲጠፊ ወይም መለወጥ ሲያስፈልግ ይዘቱን ጠብቀው ተመሳሰይነት ባለው ቁስ በማጠናከር ለዘለቄታዊ አገልግሎት እንዲውል መስቻል ያስፈልጋል፡፡
4) የጠፉ ወይም ክፉኛ የተጐዱ የቅርስ አካሎችን አስፈላጊውን አማራጭ ዘዴና ቁስ ተጠቅሞ መልሶ መገንባት ወይም መጠገን ይኖርበታል፡፡
5) ቅርሱን በማልማት ቅርሱን ወይም የቅርስ ቦታውን የሚሰጠውን ነባር ወይም አዲስ አገልግሎት እንዲቀጥል የሚከናወኑ የማሻሻያ፣ የማስፋፊያና የማስዋቢያ ተግባራትን ማካናወን አለበት፡፡

## 11.የክትትልና ቁጥጥር ሥራ

በሀገሪቱ ውስጥ የሚከናወን ማንኛውም የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ስራ በዚህ መመሪያ መርህ መሠረት እንደየቅርሱ ደረጃ በተገቢው መንገድ ስለመከናወኑ በባለሥልጣኑ ወይም በቢሮዎች ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## መብትና ግዴታ

## 12.የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ- ጥገና ሥራ የሚያከናውን ሰው መብት

1) በመስኩ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችና ድጋፎችን ከሚመለከተው አካል የማግኘት፣

2) የሰው ኃይል፣ የሎጂስቲክና የቁሳቁስ ድጋፍ ከሚመለከታቸው የዘርፉ አካለት በበቂ ሁኔታ የማግኘት፣//

## 13.<u>የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ሥራ የሚያከናውን ሰው ግዴታዎች</u>

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 የተዘረዘሩትን መርህዎችንና ዓለም አቀፍ መለኪያዎችን የማክበር፤
2) በቅርሱ አካባቢ የሚካሄዱ ማናቸውም ቅርሱን ሊጐዱ የሚችሉ እንቅስቃሴዎችን የማስቆም ወይም ለባለሥልጣኑ ወይም ለሚመለከታቸው የፍትህ አካላት የመጠቆም፣
3) ቅርሱን በጥገና ጥናት መሠረት በከፍተኛ ጥንቃቄ አከናውኖ በተገባዉ ዉል መሰረት የማስረከብ፣
4) ጥገናና ጥበቃ የሚደረግለትን ቅርስ ወይም መካነ ቅርስ እሴትና ተዓማኒነት ለመጠበቅ፣ ነባሩን ገፅታና ይዞታ እንዳይለቅ የማድረግ፣
5) በቅርሱ ላይ አደጋ ከሚፈጥርና ነባር ይዞታውን ከሚያሳጣ አሠራር የመቆጠብ፣
6) የቅርስ መረጃዎችና እሴቶች እንዳይዛቡ ወይም እንዳይጠፉ ወይም እንዳይቀየሩ ጥንቃቄ የማድረግ፣
7) ለቅርስ ጥበቃ እንክብካቤ-ጥገና ጥቅም ላይ የዋሉ የአሰራር ዘዴዎችና ቁሳቁሶች ለቀጣይ ሥራ ወይም ጥናት እንዲያገለግሉ በመረጃነት በመያዝ ለሚመለከተው አካል የማስተላለፍ፣

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የስራ ፈቃድን ስለማደስና መሰረዝ</u>

## 14. <u>የስራ ፈቃድን ስለማደስ</u>

1) የቅርስ ጥበቃና ጥገና የስራ ፍቃድ ያገኘ ሰው ተገቢውን ክፍያ በመፈፀም ፍቃዱን በ2 ዓመቱ በሚመለከተው አካል ማሳደስ አለበት፡፡
2) ፈቃድ ካገኘ በኋላ አቅርቦት በነበረው የጥበቃና ጥገና የስራ ዝርዝር ወይም የጥገና ጥናት መሠረት በትክክል ስለማከናወኑ በሚቀርቡ የመስክ ሪፖርቶች መነሻነት እድሳቱ ይከናወናል፡፡

15. <u>የሥራ ፈቃድን ስለመሰረዝ</u>

1) የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ሥራ ፍቃድ ሊሰረዝ የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች መፈፀማቸው ሲረጋገጥ ይሆናል፡-

ሀ. የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ -ጥገና የሚያከነውን ሰው ከላይ በአንቀፅ 14 የተዘረዘሩትን ግዴታዎችን ተላልፎ መገኘቱ ሲረጋገጥ፤

ለ. የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ሥራው የሚጠይቀውን ሥነ-ምግባር በመጣስ ስራውን ተገቢ ባልሆነ አሰራር ወይም የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ባልያዘ ሰው ያከናወነ ስለመሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሐ. የስራዉ ፈቃድ በተሰጠ በአማካይ ጊዜያት ውስጥ ስራዉ ካልጀመረ፤

መ. የተሰጠው ፈቃድ ከአላማው ውጭ እየተሰራበተ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሠ. በዚህ መመሪያም ሆነ በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች የተጣለበትን ግዴታ በአግባቡ አለመወጣቱ ሲረጋገጥ፤

ረ. የሥራው ፈቃድ በአመልካቹ ሲመልስ

2) የቅርስ ትበቃና ጥገና የስራ ፍቃድ ከመሠረዙ በፊት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያና እንደጥፋቱ ክብደት ምክያታዊ የማስተካከያ ጊዜ ይሰጠዋል፡፡

3) ባለሥልጣኑ ወይም ቢሮው በሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ሁኔታዎች የማይስተካከሉ ከሆነ የስራ ፍቃዱ ይሰረዛል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

16.<u>የመተባበር ግዴታ፤</u>

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ በማስፈጸም ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

17.<u>ስለቅሬታ አቀራረብ</u>

1) የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ሥራ ፍቃድ አሰጣጥ ወይም መሰረዝ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ሁኔታው በፅሁፍ ከተገለፀለት ቀን ጀምሮ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ውሳኔ ለሰጠው አካል በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ቅሬታው የቀረበለት ኃላፊ ውሳኔውን በ10 የስራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በፅሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፤ ሆኖም ግን

በሃላፊው ውሳኔ ያረካ ወገን አቤቱታውን በ10 የስራ ቀናት ውስጥ ለሚንስቴሩ በማቅረብ የመጨረሻውን ውሳኔ ማግኘት ይችላል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ዉስጥ በተጠቀሱት የጊዜ ገደብ ውስጥ ቅሬታውን ያላቀረበ አመልካች የተወሰነውን ውሳኔ እንደተቀበለ ይቆጠራል፡፡ሆኖም ቅሬታውን ሊያቀርብ ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ በበቂ ህጋዊ ማስረጃ ከተረጋገጠ ማመልከቻው ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

19.<u>*መመሪያውን ስለማሻሻል*</u>

ይህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ ሊሻሻል ይችላል፡፡

20.<u>**ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎቾ**</u>

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራሮች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም

21.<u>*ማንዋል ስለማውጣት*</u>

ባለሥልጣኑ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ማንዋል ሊያወጣ ይችላል፡፡

22.<u>*መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ*</u>

ይህ መመሪያ ከመስከረም 4 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ዶ/ር ሒሩት ወልደማርያም

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር